# የሲያትል የማመላለሻ መምሪያ (SDOT) እና የሲያትል ቤቶች ባለሰልጣን (SHA) የሕዝብ መጓጓዣ ማሳለፊያ ፕሮግራም – ጥር 2023

AMHARIC




1.2023

Seattle Department of Transportation

Seattle Housing Authority

## የSHA የሕዝብ መጓጓዣ ማሳለፊያ ምንድን ነው?

የSHA የሕዝብ መጓጓዣ ማሳለፊያ በሁሉም የSHA ባለቤትነት ይዞታ ያሉ እና የሚተዳደሩ ንብረቶች ውስጥ ላሉ ነዋሪዎች ሙሉ በሙሉ በመንግሥት የሚከፈል የORCA ካርድ ነው። የፕሮግራም ተሳታፊዎች እስከ ታሕሳስ 31 ቀን 2026 ድረስ ነፃ፣ ያልተገደበ ጉዞዎችን ማድረግ ይችላሉ። ማሳለፊያዎቹ በORCA ካርድ ወይም በአውቶቡስ ማሳለፊያ ላይ ተጭነዋል።

## ለSHA የሕዝብ መጓጓዣ ማሳለፊያ እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

አዲስ አመልካች ከሆኑ፣ እባክዎን በ www.surveymonkey.com/r/SHAIntakeForm ላይ የመስመር ላይ ማመልከቻ ይሙሉ። በ www.Seattle.gov/transportation/transitpassprogram ድህረ ገጻችንን ይጎብኙ ወይም ለበለጠ መረጃ 206.615.3551 ይደውሉ።

## አዲሱን የSHA የሕዝብ መጓጓዣ ማሳለፊያዎን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ

እስከ ታሕሳስ 31 ቀን 2026 ድረስ በሕዝብ መጓጓዣ ላይ ነፃ፣ ያልተገደበ ጉዞዎችን ማድረግ ይችላሉ። ካርድዎን በቀን 24 ሰዓት በሳምንት ሰባት ቀን መጠቀም ይቻላል።

**አውቶቡስ**: ወደ አውቶቡስ ላይ ከወጡ በኋላ የORCA ካርዱን ከአንባቢው ጋር መታ ያድርጉ። አውቶቡሱ ላይ መውጣት/መውረድ እንደሚፈልጉ ለሾፌሩ ለማመልከት መውረጃ ቦታዎ ከመድረስዎ በፊት ቢጫ ገመዱን ይጎትቱ።

**ቀላል ባቡር እና የመንገድ መኪና (Streetcar):** ባቡሩ ውስጥ ከመግባትዎ በፊት እና ለሁለተኛ ጊዜ ከባቡሩ ከወጡ በኋላ የORCA ካርዱን ከመድረኩ/ከአንባቢው ጋር መታ ያድርጉ።

## አዲሱን የSHA የሕዝብ መጓጓዣ ማሳለፊያዬን የት መጠቀም እችላለሁ?

የSHA የሕዝብ መጓጓዣ ማሳለፊያው በORCA ካርድ ላይ ተጭኗል። ካርዱን ያለምንም ወጪ በኪንግ ካውንቲ ሜትሮ፣ በኪንግ ካውንቲ የውሃ ታክሲ፣ በሲያትል ስትሪትካር፣ በሲያትል ሴንተር ሞኖሬይል፣ በሳውንድ ትራንዚት፣ በኮሙኒቲ ትራንዚት፣ በፒርስ ትራንዚት፣ በኪትሳፕ ትራንዚት እና በኤቨረት ትራንዚት ላይ ያለ ምንም ክፍያ መጠቀም ይችላሉ። ደግሞም የእርስዎን ORCA ካርድ በACCESS ላይ ወይም Via to Transit ላይ መጠቀም ይችላሉ። የORCA ካርዶካርዶቹን በዋሽንግተን ስቴት የማመላለሻ ጀልባዎች ላይ መጠቀም አይቻልም።

## ለማሰስ እገዛ ይፈልጋሉ?

በሲያትል የማመላለሻ ሥርዓት ውስጥ ለመመላለስ የሚያግዙዎት ብዙ የመርጃዎች/የእገዛ ምንጮች አሉ:

**One Bus Away:** ለአውቶቡሶች እና ለቀላል ባቡር የእውነተኛ ጊዜ መድረሻ መረጃ ለማግኘት ይህንን የስልክ መተግበሪያ ወደ ስልክዎ ያውርዱ።

**ጉግል ካርታዎች:** ጉግል ካርታዎችን በኮምፒውተር ላይ ወይም በስልክ መተግበሪያ መጠቀም ይችላሉ። ደግሞም የእውነተኛ ጊዜ የመድረሻ መረጃን ያካተተ የሕዝብ መጓጓዣ አቅጣጫዎችን ያቀርባል።

**የኪንግ ካውንቲ የጉዞ ዕቅድ አውጪ:** ለጉዞዎ የሕዝብ መጓጓዣ አቅጣጫዎችን ለማግኘት ይህንን ድህረ-ገጽ ይጠቀሙ: https://tripplanner.kingcounty.gov/

## የእኔን SHA የሕዝብ መጓጓዣ ማሳለፊያ ለምን ያህል ጊዜ መጠቀም እችላለሁ?

ያልተገደበ አጠቃቀም ማሳለፊያው በራስ-ሰር ታሕሳስ 31 ቀን 2026 በዕለተ ቀኑ መጨረሻ ጊዜው ያበቃል።

ይህ ፕሮግራም ካለቀ በኋላ የሕዝብ መጓጓዣ አቅም መቻልዎን በተመለከተ የሚያሳስብዎት ከሆነ፣ የትኛው ቅናሽ ያለው የታሪፍ አማራጭ የእርስዎን ፍላጎቶች እንደሚያሟላ ለማወቅ የኪንግ ካውንቲ ሜትሮ ድህረ ገጽን እንዲጎበኙ እናበረታታዎታለን: https://kingcounty.gov/WhichORCAFare

## የጠፋ ወይም የተጎዳ ካርድን መተካት

የORCA ካርድዎ ከጠፋ ወይም ከተጎዳ፣ እኛ ያለምንም ወጪ እንተካለን። ተተኪ ካርድ ለመጠየቅ እባክዎን ከስምዎ እና ከአድራሻዎ ጋር ያግኙን። አዲስ ካርድ በታደልዎ ጊዜ የቀድሞ ካርድዎ ይታገዳል።




**የግኑኙነት መረጃ**
**ኢሜይል:** TransitPass@seattlehousing.org
**ይደውሉ/የጽሑፍ መልእክት:** 206.615.3551
**ድህረ ገጽ:** www.seattle.gov/transportation/TransitPassProgram